In his hubris, without knowing it, has Tang hit upon something? Stewart was found guilty in 2004 of conspiracy, obstruction of an agency proceeding, making false statements to federal investigators. Stewart served a five-month term. Without even going to trial yet, Tang has already served three months --after being denied bail. "Martha Stewart, Lehman, Fannie Mae, Freddie Mac, Goldman Sachs! They cheat the system much more. They cheat the American people and taxpayers. But they are getting off free, while I am charged, my business and life destroyed." Tang sighs and shrugs his shoulders in despair.

Ironically, whether self-serving or not, Tang's comments about his new crusade as the "anti-fraud," may one day be seen as one of the tipping points of public awareness and patience, that helps better the financial industry and world; exposing the corruption, and unaccountability of some global government and corporate leaders.

Over these years, we have written about such evil. For over a decade, there have been much more brilliant minds making such similar warnings about the implosion of the American and global financial system; like whistle-blower, Catherine Austin-Fitts, a former managing director, and a member of the Board of Directors of the prestigious Wall Street investment bank Dillon, Read & Co., Inc.

Austin-Fitts served as Assistant Secretary of Housing/Federal Housing Commissioner at HUD, in the first Bush Administration. For years, she warned about missing trillions of dollars; warned openly about these mega-holes and manipulations in government and corporate financing.

Bernie Madoff, a former NASDAQ Chairman; Fannie Mae, Freddie Mac, Enron, Lehman, Merrill Lynch, AIG, Goldman Sachs... The politicians, the bankers, brokers, lawyers, accountants who enabled them.

Activists and concerned citizens across North America and around the world are now trying to act, to raise the global consciousness of the peoples of the world.

Adding "fuel" is mega-corporation, BP, British Petroleum, its Gulf oil spill destroying the precious water, ecology and lives of people of Canada, USA and the world. Through its lobbying, American politicians set BP's maximum liability for oil spills at $75 Million USD... The stakes are high for the world, in this struggle against corporate and government accountability. For Tang, the stakes are high, too, he faces 60 years of prison, if convicted.

So we come full circle, in the larger than life, but true world and mind of Mr. Weizhen Tang, the Chinese Warren Buffett, or the Chinese Bernie Madoff; with a twist of Martha Stewart, and a dash of Donald Trump hubris...




**Local(Canada) .................. $35.00**
**USA ............................. $45.00**
**Others .......................... $65.00**
**Institution...................... $100.00**

To Place an ad, please call **416- 459-5964**

or email us at: **Hawarya.publications@sympatico.ca**

# የተቃውሞ ሰልፍ ተካሄደ




ወደ ቶሮንቶ (ካናዳ) የዘለቁትን የኢትዮጵያው ገዥ ሥርዓት ተወካዮችን በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ተደረገ። ሰላማዊ ሰልፉን በጋራ ያዘጋጁት የኦጋዴን አካባቢ ተወላጅ ኢትዮጵያዊያንና ራሳቸውን ኦሮሞ-ካናዳዊያን ማህበረሰብና ለሰብአዊ መብቶችና ዴሞክራሲ አንድነት (Oromo-Canadian Community, and, Unity for Human Rights & Democracy) በሚል የተሰባሰቡ ወገኖች ሲሆኑ ከአንድ መቶ የማያንሱ ተቃዋሚዎችን ማሰለፋቸውን ከቦታው ተገኝተን ዘግበናል።

ተቃዋሚዎቹ ከያዙዋቸው መፈክሮች መካከል ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ግድያ ይቁም፣ ደም የተጠማ አምባገነንን እንቃወም፣ ፍትህ ለተበደሉ፣ ወዘተ .. የመሳሰሉት የተስተዋሉ ሲሆን የመለስ ዜናዊን ስዕል ከጀርመኑ ፋሽስት ጋር በማነጻጸር “ጥቁሩ ሂትለር” የሚል ስያሜ የተሰጠው ሰሌዳ ከፍ ብሎ ተይዞ እንደነበርም መመልከት ተችሎዋል።

በእለቱ ከተሰራጩት በራሪ የተቃውሞ መግለጫዎች እንደተገለጠው በቶሮንቶ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን ለማነጋገር ከመጡት የኢትዮጵያው አምባገነናዊ ሥርዓት ተወካዮች መካከል የፌዴራል ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ አባይ ጸሃይ ይገኙበታል ቢባልም የእንግዶቹን ማንነት በእለቱ ማረጋገጥ አልተቻለም። ለየት ካሉ ምንጮች እንደሚደመጠው ከሆነ የእንግዶቹ አይነት በካናዳ የኢትዮጵያ ኤምባሲ የተመራ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከሌሎች ክፍሎች የተላኩ ዝቅተኛ ባለሥልጣናት ሳይሆኑ እንዳልቀሩ ተገልጹዋል። የእንግዶቹ አላማ ኢትዮጵያ የምትገኝበትን የእድገት ጎዳና ለማስረዳትና በተለይም በአሁኑ ሰአት የእርሻውን ክፍለ ኢኮኖሚ የልማት ዘርፍ አስመልክቶ ስለሚገባው የውጭ ኢንቨስትመንት ለማስረዳት እንደሆን ተጠቅሱዋል።

የተቃውሞ ሰልፉን በመተባበር ያዘጋጁት ወገኖች በየግላቸው የተቃውሞ በራሪ ወረቀቶችን ያሰራጩ ሲሆን፣ በኦሮሞ-ካናዳዊያን የተበተነው ሰፋ ያለ መልእክት አካቱዋል። ላለፉት በዛ ያሉ ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ በኦሮሞ ተወላጆች ላይ እየደረሰ ያለውን አሰቃቂ በደል በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ የሰባዊ መብቶች ተቆርቋዋሪ ድርጅቶች የዘገቡትን ዋቢ በመጥቀስ አትቱዋል። አሁን በቅርቡ ማርች 31/2010 ፍትህ የጎደለው የሥርዓቱ ፍርድ ቤት 16 (አስራ ስድስት) የኦሮሞ ተወላጆችን በሞት፣ እድሜ ይፍታህና ለረጅም ጊዜ እስራት ዳርጉዋል ይላል። ለኦሮሞ ህዝብ መብት መከበር የኦሮሞ ነጻ አውጭ ግንባርን (ኦነግ) እንቅስቃሴ በአውንታ የሚጠቅሰው ይህ የተቃውሞ በራሪ ወያኔ/ኢሃዴግ የኦነግን እንቅስቃሴ ለመግታት ከመሻት ባሻገር ጭራሹን ለማምከን ገዥው ድርጅቱን በህገ-ወጥነት ፈርጆ እንዴት በላዩ ላይ የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦዴድ) የተባለ ተለጣፊ እንደፈጠረበት አትቱዋል። ኦህዴድ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ጭራሽ ተቀባይነት እንደሌለው የሚያስምርው ይህ በራሪ የተቃውሞ መግለጫ የሥርዓቱን ፖሊሲዎች የማይቀበሉ ኦሮሞዎች የኦነግ ደጋፊዎች ናችሁ እየተባሉ እየደረሰባቸው ያለውን መሳደድ ከማተቱ በላይ በ1991 እና 2000 ዓ.ም መካከል ብቻ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ አምስት (2585) ህገወጥ ግድያዎች እና ስምንት መቶ ስድሳ አምስት (865) የደረሱበት የጠፋ ወገኖች በሰባዊ መብቶች ተቆርቁዋሪ ድርጅቶች አመካይነት የተጠናቀረ ሰነድ እንደሚያስረዳ አስፍሩዋል።

በራሪው መግለጫ በማያያዝም የኦሮሞ ተወላጆች በአሁኑ ጊዜ አዲስ የማጥፋት ዘመቻ እየተካሄደባቸው እንደሆነ ሲጠቅስ በውጭ ኢንቨስትመንት ሰበብ ተወላጆች ከአያት ቅድመ አያቶቻቸው ከወረሱት መኖሪያ ቦታ በግድና በሃይል እየተፈናቀሉ መሆኑን በምሬት አስረድቱዋል። ይህን ድርጊት የበለጠ ትርጉዋሜ በመስጠትም “የረጅም ጊዜ እቅድን ተግባራዊ ለማድረግ በዘዴ ዘርን ለማጥፋት የሚካሄድ መመሪያ ነው” ይለዋል።

በሌሎቹም የተበተኑት በራሪ የተቃውሞ መግለጫዎች በየበኩላቸው ልዩ ልዩ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች የዘገቡዋቸውን መረጃዎች ዋቢ እያደረጉ በኢትዮጵያ ውስጥ እየደረሰ ስላለው የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥሰት ሰፋ አድርገው አትተዋል።

# የይስሙላ ምርጫ

በግንቦት 2002 ይደረጋል ተብሎ ብዙ የሚባልለት ምርጫ ከወዲሁ የአሸናፊው ማንነት የታወቀ ነው። ወያኔ/ኢ.ህአዲግ ይህንን ምርጫ የሚያደርገው በታሪክ አጋጣሚ ስልጣን በተቆናጠጠ ማግስት ለዓለም አቀፍ ተቀባይነት ሲል ብቻ ሕገ መንግስት አርቅቆ በህዝብ አጸደኩ በማለት እራሱ በወጣው ህገመንግሥት አስገዳጅነት ከላይ እስከ ታች የራሱን አሻንጉሊቶች በአስመራ ጭነት ሰይሞ በየአምሥት ዓመቱ ዓለምን በማሞኘት ላይ ይገኛል።

ኢ.ህአዲግ በማንኛውም ዓይነት መንገድ በመጠቀም ሥልጣኑን ሊያራዝምለት የሚችለውን መንገዶች መሰሪ ተንኰሎችን በመቀያየር አሁንም ለምርጫ 2002 የተለመደውን የድምጽ ስርቆት በተግባር ለማዋል ዝግጅቱን አጠናቋል።

በምርጫ ’97 ውጤቱ ለወያኔ አስደንጋጭ ሁኔታዎች ፈጥሮ ማለፍ ኢ.ህአዲግ ከዚህ ያልተጠበቀ ቅሌት መማር የሚችለውን ተምሮ በተጨማሪም የአለም አቀፍ ሁኔታዎችንም ለእሱ የማይመቹ ቢሆንም ነገር ግን እንዲመቸው ለማድረግ ጠንክሮ በመሥራት ላይ ነው።

በመሆኑም የአሁኑ የመጨረሻው የወያኔ መልካም አጋጣሚ የሆነለት የአንድ አመት እድሜ ያስቆጠረው የአሜሪካው የኦባማ መንግስት አቅጣጫ ከጅምሩ ከሙስና ያልጸዱ እና ዲሞክራሲን በትክክል የማይተገብሩ የአፍሪካ መንግስታት እና መሪዎቻችው አይስማሙኝም የሚል አቋሙን ገልጸ የነበረ ቢሆንም እምነቱን በኢ.ትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ ተስኖት በሶማልያ በየመንና በመታየት ላይ ያለው የአሸባሪዎች እንቅስቃሴ ኢ.ህአዴግን በጥንቃቄ በተቃና ጥበብ የማቆየት አሥፈላጊነት ከመጋርጃ ጀርባ የአሜሪካ መንግስት ፍላጎት ይንፀባረቃል።

በዚሁም መጠን ትግሉ እንዲቃጠል ለማድረግ ወሳኝ ነን በሚሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎቻቸው በዓላማቸው ፅንተው ኢ.ህአዲግን ሊያንገደግድ ወይም ሊገለብጥ የሚችል ኀይል መፍጠር አቅም አንሷቸዋል።

ስለሆነም የተቃዋሚ ፓርቲዎች እና የኢ.ትዮጵያ ህዝብ ትግሉን አጠናክሮ ይህ ምርጫ ሳያታልለው የጠቅላይ ሚኒስትር መለስን መንግስት ከሥልጣን ለማስወገድ የተጠናከረ ትግል እና አንድነት ይጠበቅበታል።

በመጨረሻም ኢ.ህአዲግ በኢ.ትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሰውና እያደረሰው ያለው ኢሰብአዊ ግፍና በደል በህዝቡ ውስጥ ተደፍኖና ታምቆ የሚፈነዳበት ቀን መምጣቱ የማይቀር መሆኑን ነው።

ኤልያስ መንገሻ
ሂፐንሃይም
ጀርመን

TANA
TANA PRINTING ENT.
ጣና ማተሚያ ቤት
ማንኛውንም የህትመት አገልግሎት በየትኛውም ቋንቋ እንሰጣለን።
Complete Printing & Copy Services Including Wedding Invitations

2,500 Full Color Business Cards (Both Sides) $125
5,000 Full Color Business Cards (Both Sides) $199
10,000 Full Color Business Cards (Both Sides) $375

Limited time offer
633 Vaughan Rd. Toronto ON. M6C 2R4 (Vaughan & Oakwood)
Tel: 416.654.2020
Fax: 416.653.6191
e-mail: print@tanaprinting.com
website: tanaprinting.com

LAW OFFICE
JOSEPH OSUJI
B.A (Hons), LLB
Barrister, Solicitor & Notary Public
The Law office is accepting new clients for:
- Criminal Law
- Police Complaints
- Family Law
- Immigration law
- Refugee Law
- Civil Litigation
- X Human rights/Discrimination.
- Business/commercial Law
- Native Law
- Coroners' Inquests



Fearless, Aggressive, Fight To Win Justice
Cell: 416-559-1418
Office: 647-349-5225
Fax: 647-349-5355

# ከ ዜ ና ው ባ ሻ ገ ር

ከገጽ 5 የዞረ

ካላሸነፍኩ ዴሞክራሲ የለም ሲል የተደመጠ ነውና “ወይ ለይ ና ጉድ ፈሊኡ” (ቃልሲና መሪር እዩ?) ሁኔታ የሚጠበቅ ሆኗል፡፡ መለስ ዜናዊ ሁሌም ሌሎች ሲያሴሩበትና ሻጥር ሲያዘጋጁበት የሚታየውና የሚቃዥም ፈሪ በመሆኑ ጡት አባቱ አሜሪካ በለሆሳስ ወረፍ ሲያደርገው እሱ ግን እየተዘጋጀ ያለን ተንኮል እያውጠነጠነ መራዱ ይታያል፡፡ አሜሪካ መቸም ቢሆን በመለስ ዜናዊ ላይ የረባ ጫና ስታደርግ ያልታየች ቢሆንም ባለፈው ሰሞን በእጅ አዙር (በሰብዓዊ መብት ተከላካይ ተብዬ ተቋም አማካይሠነት) ወያኔን መውረፏ፤ ብርቱካን ሚዴቅሳን የፖለቲካ እስረኛ ማለቷ፤ በምርጫው ግዜ አስጊ ሁኔታ ይኖራልና ወደ ኢትዮጵያ ጉዞን በሚመለከት ለዜጎቿ ማስጠንቀቂያ መስጠቷ ሁሉ ለወያኔ የወዳጅ ሥራ፤ቀና አቅዋም መስሎ አልታየውም፡፡ ስለዚህም ይርዳል፤መለስም ጫጫታ አብዝቷል፡፡ ለየት ያለን አቅዋም በጠላትነት መፈረጅ ወያኔነት መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡ ወያኔ በዋሺንግተን ዲሲ በተካሄደው የአፍሪካ ቀንድ ሰብሰባ ላይ ሁሉ ኡኡታ ማሰማቱ ከዚሁ ስጋቱ ጋር የተያያዘ ነው (ለነገሩማ ጉባዔው ጊዜ ያለፈበትን ከወያኔ ጋር ዕርቅና ወያኔ ያለበት

አዲስ የሽግግር መንግስት ይመስረት የሚል አቅዋምን ያስተጋባ ሆኖ ተደምድሟል)፡፡

“ዋፒንዴ ዋሲፒንዴ” እንዲሉ ኬንያዋያን (ማለትም ወጣም ወረደም በኛው ቋንቋ) የአገዛዙ ችግር መሰረታዊና ዘላቂም ነው፡፡ በቅርቡ በሻዕቢያ የተላኩ 10 የሶማሌ ተወላጅ አሸባሪዎችን ይዣለሁ ሲል ለራሱ የሚበጀውን ግን ሊጣራ የማይችል መረጃ አልባ ልፈፋውን አስደምጧል፡፡ ዛሬ ወያኔ ሊደብቀው ያልቻለው ጉዳይ ግን በኦጋዴን ብዙ ቦታዎች ከባድ ውጥረት መኖሩንና የመኪና ጉዞ ራሱ እያስቸገረ መምጣቱን ውስጠ አዋቂዎች አጋልጠዋል፡፡ የአስር ሰዓት ጉዞ ዕድሜ ለወያኔ

የተጠናከረ ኬላና ፍተሻ ሶስት ቀን እየፈጀ መምጣቱ ታይቷል፡፡ በሐረር ከተማ የሶማሌ ተወላጆች በሚኖሩበት ቦታም ፍተሻው በዝቷል፡፡ በጎንደርም ቢሆን “ሽፍታ” እየተባለ ያለው እንቅስቃሴ መጠቀስ ያለበት ነው፡፡ በዚያ ይንቀሳቀሳል ይባለ የነበረው የአርበኞች ግንባር ይዘት ግን አነጋጋሪ መሆኑ አልቀረም፡፡ ይህ ድርጅት ተቀማጭነቱ አስመራ ( በተጨባጭ ተሰነይ አጠገብ ጦር ሰፈር አለው ተብሏል) ነውናም ከሻዕቢያ ጣልቃ ገብነት ነፃ መውጣት ከብዶታል ይባላል፡፡ ለሻዕቢያ ያልተስማሙ መሪዎቹ ተወደደም ተጠላም ይነሳሉ ወይ ከጥቅም ውጪ ይሆናሉ ሌሎች ለአስመራው አዛዥ ናዛዥ አቅዋም ተገዢ ናቸው የተባሉ ይሾማሉ የሚል ክስ አለ፡፡ የኢአግ አባል የነበረውና የዚህ ግንባር መሪነኝ ይል ከነበረው ግለሰብ ጋር ተጋጭቶና ተበሳጭቶ ወደ አስመራ

ያቀናው ተማሪ ተስፋዬ ጌታቸው በሻዕቢያ መገደሉ ሲጠቀስ የደርግ ኢሰፓ አባል የነበረው

የአየር ኃይሉ ኮለኔል ታደሰ ደግሞ ከግንባሩ ተገልሏል፡፡ በጀርመን ነዋሪ የሆነውም የግንባሩ

መስራች መስከረም አታላይም ቢሆን ተመሳሳይ የመገለል ሁኔታ ተጭኖበታልም ተብሏል፡፡

በቅርቡ ደግሞ የግንባሩ መሪዎች በበቂ ታዛዥ ባለመሆናቸው ቢያንስ 17 የአመራር አባሎች

(ከነዚህ ዋነኞቹ ለሻዕቢያ ያደሩ፤ ለስለስ ያሉና ባዕድ ሀገር ያሉ ናቸው ተብለዋል) በግንባሩ

አመራር ኮሚቴ እንዲገቡ ተደኗል፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ የአርበኞች ግንባር ሰፋ ብሎና ተጠናክሮ መንቀሳቀስ ሲገባው በውስጡ በጦር መሪነት ተመድቦ የነበረው ኮለኔል አለበል አማረ (በ1997

የአግአዚ ጦር መሪና በተፈፀመው ግድያ አንዱ ተጠያቂ) ከግንባሩ ወጥቶ የራሱን የአማራ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ መመሰረቱን የአስመራ ቴለቪዢን አሳይቶናል፡፡ ለምን በብሄረሰብ ደረጃ የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባርን መከፋፈል ተፈለገ? ለምን ይህ ግንባ ር እንዳይጠነከር ተደረገ ? ሻዕቢያ ኢትዮጵያን የመከፋፈል ዕቅድና ምኞት የለውም የሚሉን ዛሬ ምን ይሉ ይሆን? ብዙ ጥያቄ አለ ግን ወያኔ ከአርበኞች ግንባርና ከአስመራ በኩል የሚያሰጋና የሚያስፈራ ጥቃት ሊመጣብኝ ነው በሚል ስጋት ላይ አለመሆኑን ውስጠ አዋቂዎች ይናገራሉ፡፡ ግን ይህ ማለት ወያኔ ስጋት እያገላበጠው አይደለም ማለት ሊሆን አይችልም፡፡

የተቃዋሚ ድርጅቶች ይዘትም የወያኔን ድንጉጥ መሪ ትንሽ ሊያረጋጋው በተገባ ነበር፡፡ በየአቅጣጫው የሚታየው ክፍፍልና ንትርክ ወያኔ ላይ ያነጣጠረ አይደለም፡፡ የሰላዩ ጌታቸው አሰፋ

ምልምሎች በየድርጅቱ ሠርገው ገብተው የሻጥር ከበሮአቸውን እየደለቁ ናቸው፡፡ መኢአድ

ምርጫ እገባለሁ ካለ ጊዜ ጀምሮና መሐንዲሱ አቶ ኃይሉ ሻውል ከመለስ ጋረ ሲጨባበጡ ከታዩ ጊዜ ጀምሮ ወያኔም ባሽከረከረው አሉባልታ ታግዞ በተፈጠረው ጥርጣሬና ንዴት ድርጅቱና መሪው የተጠበቀውን ድጋፍ አገኙ ወይም ሊያገኙ ይችላሉ ማለቱ ከባድ ሆኗል፡፡ ድርጅቱ አቅዋሙን አሳማኝ በሆነ መንገድ ለሕዝብም በበቂ አስረድቷል ማለት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል መድረክ

የተባለው ስብስብ በአይታክቴው በየነ ጴጥሮስ አማካይነት (የሀገሪቷ ፕሬዝዳንት ሆኖ ለመመረጥ ሞክሮ፤ አቤት መቋመጥ፤እንደተጠበቀው ሲወድቅ በሀገሪቷ ዴሞክራሲ የለም ያለው!) መጪው ገዢ ፓርቲ እንሆናለን ቢልም፤ ስዬ አብረሃም ቢያንስ በተምቤን አሸንፋለሱ ብሎ ቢፎክርም

መጨረሻው ያማረ ለመሆኑ ብዙም ተስፋ የለም፡፡ ትላንትን ረስተው በድኗጅት ቱሪስትነት ዛሬ

ደግሞ የነስዬ አጫፋሪና ደጋፊ የሆኑ ክፍሎች (አንዳንዶቹ ሳልሳዊ ወያኔን ተመኚዎች) ከላይ በፃፍኩት ላይ ኡኡ ማለታቸውን ብጠብቀውም ሀቁ ግን መድረክ በትግራይም ሆነ ሌላ ቦታ ሊያሸንፍ የሚችለው ወንበር ወያኔ በበጎ ፍቃዱ የሚለቅለትን መሆኑን መካድ የሚቻል አይደለም፡፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ መድረክን የተደባለቁት ስዬና ገብሩ አስራት፤ ቀይ ሽብር ነበረ እንዴ ብሎ የካደውና ፍትህ ቢኖር ኖሮ ለፍርድ መቅረብ የሚገባው ኢሰፓው ዶክተር ኃይሉ አርአያና ሌላው ኢሰፓ መሀንዲስ ግዛቸወም ቢሆኑ ሕዝብ ብዙ የሚጠይቃቸውና አመኔታም የሚሰጣቸው አይደሉም፡፡ አሌ ብለው የሚጮኁ ጥቂቶች፤ በተለይም በባዕድ ሀገሮች– ሊኖሩ መቻላቸውን ባውቅም ማለቴ ነው፡፡ የሞትን መጥፎነት በመጀመሪያ አዋቂው ሟቹ ነው እንበልና ለቀይ ሽብር ወንጀለኞች ሆኑ ሌሎች መሰል ተጠያቂዎች ቸልታ የሚያሳዩትና ምህረት ለምንስ ጠይቀው ባይነትን የሚያሰሙ ወይ በወንጀሉ የተሳተፉ አሊያም ያልደሙና ያልተሰቃዩ አሊያም ሰማዕትን የካዱ ናቸው ማለትም ትክክል ነው፡፡ ወደ ድርጅቶቹ ስንመለስ ግን ውህደትና ቅንብራቸው ወይም

ጥንካሬያቸው ከ1997 ጋኗ ሲወዳደር አመርቂ አይደለም፡፡ የአንድነት መሪ ለቃሊቲ ተዳርጋ

ወደ ገጽ 19 ዞሯል


## Jagama's Accounting Services

**We do ...**

- TAX RETURNS
- COMPUTERIZED BOOK KEEPING
- BUSINESS CONSULTING
- LOAN APPLICATION

**During Tax Times ..**

- WE DO ELECTRONIC FILING(EFILE)
- YOU WILL GET YOUR TAX RETURN FASTER WITH THE BEST PRICE

- CALL US, FAX US, OR MAIL YOUR DOCUMENTS
- WE WILLTAKE IT FROM THERE
- SATISFACTION GUARANTEED!!

Call Jagama Gobena (Accountant) at:

**Tel. 416-588-5728**

**Fax: (416-588-9634**

**Address: 344 Marguerettta St.**



## አርሴማ ገበያ

## ARSEMA'S VARIETY

የሠርግ፥ የልደት፥ የክርስትናና ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ቪዲዮ እናነሳለን፡፡ ቡና፥ ቅመማቅመም፥ ዱቄት፥ ቅቤ፥ በርበሬ፥ አምባሻ፥ ሽሮ፥ ቆሎ፥ ጠጅና ጠላ የመሳሰሉትን ምግቦችና መጠጦች እናቀርባለን፡፡

ቪዲዮ ካሴትና እንዲሁም ሲዲ ኦዲዮ ካሴት፥ ማከራየት፥ መሸጥና መገልበጥ፥ እንሠራለን፡፡ የባህል ጌጣጌጦች፥ ልብሶችና መጽሄቶች አ ሉን፡፡

እንዲሁም ካባ በመልካም መስተንግዶ የምናከራይ ሲሆን ደምበኞችን ይሆኑ ዘንድ በትህትና እንጋብዝዎታለን፡፡




**813 Gerrard St. East Toronto, Ontario**

**Tel. (416) 461-6766**

# FESTIVAL FOCUSES ON INTERACTIVE MEDIA & DESIGN



Glimpses from the earlier FITC 2010 Interactive Media & Design show

North by Northeast (NXNE) becomes a seven day event this year, with the addition of a brand new interactive media show – NXNE interactive – to the already fascinating annual line-up of 625+ concerts, 40+ music - films and 15+ conference sessions. The 16th edition of the festival takes place in Toronto, Canada from June 14-20, 2010. NXNE interactive (NXNEi) is pleased to announce the running of the Interactive arm of the media festival from June 14 until 16th, in conjunction with world-class interactive event producers FITC. The FITC 2010 Design & Technology Festival took place recently at Hilton hotel in downtown Toronto from April 24th until April 27th. FITC (Flash In The Can), an Interactive media show running regularly every year caters to web designers, graphic designers, flash programmers, multimedia artists, visual artists, illustrators etc. It has grown into an international celebration of the world's top interactive talent. Now, the NXNEi organizers with FITC are all set to bring best of the Presentations from the world of Interactive design and media.

Interactive June 14-16 : 2010 marks the kickoff year of the first ever NXNEi component of the festival; an interactive media conference and workshops programmed in conjunction with FITC to bring the key players in new media innovation for featured talks, frank discussions and community - voted panels. Music June 16-20 : NXNE is the Canadian festival destination for new and emerging music talent featuring unsigned bands, indie favourites, and major - label headlining artists from Canada and around the world and showcases opportunity for the best in new music. Film June 16-20 : NXNE screens 40+ films from around the world at the National Film Board of Canada's Mediatheque screening centre. Bringing the best in music - centric films, selections include documentaries, dramas, comedies putting focus on the international language of music. Conference June 17-20 : The NXNE Conference draws over 2,500 industry delegates for 25+ Conference Village sessions which include celebrity interviews, networking sessions, and music-business panels. Charity June 20 : The annual 11on 11 full field soccer match pits the "Rockers" against "The World." All proceeds of the event go to support Right To Play, an international humanitarian organization whose goals are to create a healthier and safer world through the power of sport and play.



Jatin Naik
njatin@yahoo.com

North by Northeast (NXNE) announces new speakers and presentations for the inaugural NXNE interactive around the city of Toronto. Confirmed Presenters & Speakers include : Ze Frank, James Eberhardt, Simon Conlin, Daniel Schutzsmith, Duane Brown, Patrick Haney and many more etc.. Some of the presentations include : Social Media Circle Jerking 101, Community Saved The Radio Star, Consumers becoming Creators: The Future Of Music is Interactive, Viral Marketing: It's About Visibility, See?, UnMarketing: Stop Marketing, Start engaging Social media in a Virtual World, Marketing to Connect – Workshop, At the Heart of It: Struggling Hero, WordPress, Architects of Community, How to Promote Yourself Online like a Rock Star – Workshop and many others.

Now in its 16th year, NXNE 2010 has five key components: music, film, interactive, conference and charity. It puts 625+ international and local bands on 50 stages, screens 40+ films, populates Conference village sessions with groundbreakingkeynotes and inspired panel discussions, and breaks ground in the interactive media arena. FITC on the other hand has hosted large number of events through 30 cities, eight countries since the past 9 years. From Flash to motion design, Flex to AIR, design to inspiration, the event serves to challenge, inspire and educate everyone. In its 9th year, FITC Toronto event is one of its kind engaging some of the best presenters from the Industry leaving people inspired, energized and awed wanting for more. In addition to Toronto, FITC has presented events in many other cities too such as Amsterdam, L.A., Seoul, Tokyo, Winnipeg, Chicago etc.







# ጎድን ወያኔ..! ጎድን ቄጤማው..!

# አሽሙር

## ሚካኤል ምስግና

... ጭፍግግ ያለ አስቀያሚ ቀን ነው፡ ፤ ደመናው ከብዱዋል። አልፎ አልፎ ካፊያ ዝናብ ይጥላል። እንደ ግሪጎሪሳዊያኑ አህዛዊ ስሌት ኤፕሪል 15 -04-2010 ዓ.ም የግሎባላይዜሽኑ አየር ንብረት (climate) ተቆርቁዋሪው ወዲ ዜናይ ወደ ሀገረ ብሪታኒያ "ቡኪንግሃም ፓላስ" በቅርቡ አምርተው ነበር አሉ። አቻምና "ኦነግን አጠፋለሁ በማለት "የባሌ ደኖች" ላይ እሳት የለቀቁበት የአየር ንብረት ተቆርቁረው ጎይታይ መለስን ባእድ ፈረንጅ ዛሬ "ቀይ ስጋጃ" አንጥፎ "ከሮም መልስ ወደ ፓሪስ-ከፓሪስ ወደ ብራሰልስ" እያለ ኑልኝ ..! በእርስዎ መጀን ....!ሲላቸው ባዕድ (ነጭ) ሞኘ ..! ተላላ..! የሚመስላቸው በቦለቲካው የስልት ቀመር ደናግል የሆኑትን ጎምቱዎችን ትተን አውቀናል በቅትናል በማለት ከህዝብና ከሀገር ጥቅም ይልቅ ለራሳቸው ለወዲ ዜናይ ረዥም እድሜ ሻማ በማብራት ""በደንገጡርነት" ጭምር ዘብየቆሙት "ምሁር" ተብዬዎችንም ያጠቃልላል" ሲሉ በእመንነት የሚያሰምሩ በቦለቲካው ዓለም ታዛቢ (ዋችዶግ) የሚባሉት የሚያብጠለጥሉት ጉዳይ ነው።

በረዥሙ የነጻነት ጎዳና ትናንት በወርቅ ማዕድን በቀበተችው በደቡብ አፍሪካ አውሮጳዊያኑ "መጽሃፍ ቅዱስ" ጨብጠው በሮቢላን (በጢያራ) በሉት በታንኩዋ ተሳፍረው በገዛ ሀገሬው ጥቁር ላይ የነጭ የባሪያ ፈንጋዮች ባለቤቶች በመሆን ነጮች "ኔልሰን ማንዴላን" ሦስት አሥርት(ሠላሳ ዓመታት) በጉሮኖ ውስጥ አጉረው በመልቀቅ ዛሬው የክብር መጎናጸፊያ ቢያለብሱዋቸው በባሪያ ፈንጋዮች ቤት-ሣይዳ በሀገረ ብሪታኒያ ሐውልት ቢቆምላቸው ማንዴላ ሁሉንየሚረሱ ተላላ..! ፍጡር የሚመስሉዋቸው ነጮች በቁጥር አነስተኛ አይደሉም" ሲሉ በምበመቁዋጠር ይልቁኑ "ጎሽ ለልጅዋ ስትል ተወጋች" እንዲባል ማንዴላ ያለእውን ሁሉ በመርሳት ለጥቁር ህዝቦች መጻዒ ህይወት ሲባል የወሰዱት የመቻቻልን አቁዋም ያንጸባርቃል" በማለት የሚያሰምሩ ክፍሎች ይደመጣሉ። አንዳንድ አቃቂረኞች የማንዴላን"፡ ስብዕና" በመፈተሽ ዛሬ የግሎባላይዜሽኑን ዓለም የቦለቲካና የኤኮኖሚ መዘወሩንበመቆጣጠር ዓለምን እንዳሻቸው የሚያሽከረክሩትን "ቀለብ ሰፋሪዎች" ማንዴላ ለመንበሩ ከበቁም በሁዋላ ምን አይነት ሀገራዊ አቁዋም ማራመድ እንዳለባቸው በቀጭኑ ሽቦ(በስልክ) ጭምር ተዕዛዝ ለመስጠት በመዳዳት አንድጊዜ ወደ ትሪፖሊ(ሊቢያ) ጎራ በማለት ከመሪሄ መንግሥት አቻቸው ከኮሎኔል ጋዳፊ ለመምከር በዘየዱበት ወቅት (ኮሎኔሉ ከአሸባሪነት ሊስት ውስጥ እስከተወገዱ ድረስ) ቃዳፊ የማይታመኑ በመሆናቸው "ኮሎኔል ቀጣፊ" ነበር የሚሉዋቸው) ማንዴላ ወደ ትሪፖሊ እንዲያቀኑ ድፍረት አዘል ምክር ቢጤ በመለገሳቸው ማንዴላ የጨለማው ዘመን "ሞግዚትነት (ኬርቴከር) መጋረጃ ተዘግቱዋል" በማለት የሰጡት ምላሽ የሚዘነጋ አይደለም በማለት በማተት በአንድ ወቅት የፋርስ ባህር ሰላጤው "የዘይት ጉድጉዋድ ሽሚያ ግብግብ ወቅት የቀድሞው የሀገረ ብሪታኒያ "የሌበር ፓርቲው አበጋዝና የሀገሪቱ ጠ/ሚኒስትር "ቶኒ ብሌየር" ከዩናይትድ ስቴትስ ጎን በመሆን ያራምዱት የነበረው አቋምና የዲስኩር ውርጅብኝ በመቃኘት "ቶኒ ብሌየርን" ከእንግሊዝ ጠ/ሚኒስትርነት ይልቅ "የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር" ቢሆኑ ያምርቦታል ሲሉ ያወረዱትን ምጸት በመንተራስ የማንዴላ የመተማመን ስብዕና አሻራ ያንጸባርቃል" በማለት የሚተቹ አቃቂረኞች በሌላ በኩል አይጠፉም።

ወዲ ዜናይ ግን ከሀገርም ከትውልድም እርቀው ለባዕዳን የባሪያ ፈንጋዮች ጥብቅናቆመው "ጌታዋን የተማመነች በግ ምኑዋን ውጭ ታሳድራለች" እንዲሉየተሰጣቸውን ቆሻሻ ቆሻሻ የቤት ሥር አበመተወን ባዕዳን አንድ ቀን መዳልት ቁዋጥረው ስልትን በየፈርጁ ቀምረው ከቦለቲካው ማማ ላይ አሽቀንጥረው ገለል...!እስኪያደርጉዋቸው ጊዜ ብች አነው» ለምን...? ቢባል ድንበር ዘለሉ ባዕድ "ዘላቂ ጥቅም እንጅ ዘላቂ ወዳጅ የለኝም" ..! የሚል ዴዜዴራታ ስላለው ነው ሲሉ የሚያሰምሩ አጠንጣኞች በሌላ በኩል አይጠፉም። ከፊሎቹ ደግሞ ዛሬ በሰባዊ መብት ረገጣና በጂኖሳይድ (በዘር ፍጅት) የተከሰሰውና "አሥራ ዘጠኝ ዓመት ሙሉ አንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር" ያለው ወያኔ/ኢሂሃዴግ በቅርቡ "ከቀለብ ሰፋሪዎቹ" ጋር የጀመረው የቦለቲካ እሰጥ-አገባ የመጻኢ መካነ መቃብሩን ቁፋሮ ያመለክታል" በማለት ጎድን ወያኔ...! የሚሉም አሉ።

በቅርቡ ለመጻዒው ምርጫ ቅድመ መሰናዶ በወያኔ/ኢሃዴግ ቴለቪዥን በተደረገው "በዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ የውሽ ግንኙነት" የውይይት ርዕስ ላይ የቀድሞው የህዲሽ ዕምባባ ከንቲብ ዓቶ አርከበ ዕቁባይ (አለያም ነፍጠኛው "አርካበ አምቦ ውሃው" ነው የሚላቸው? ተግኝተው ነበር አሉ። ከቀድሞው ፕርተዚዳንትና ከዛሬው የዚምቦቤ አራሽ ገበሬው ከጉዋድ መንግሥቱ ዲስኩር የሚለዩት "አርካበ አምቦ ውሃው" ኒሻን ደርድረው ባለመታየታቸውመሆኑንበማስመር የቤት ልጃቸው የነበረው "የቡርቃ ዝምታው" ጥሃፊ "በጋዜጠኛው ማስታወሻ" እንዳሰመረው በውይይቱ "ኢሃዴግን" ወክለው የተሰየሙት አቶ ሬድዋን ሁሴን እና የቀድሞው የህዲሽ ዕምባባ ከንቲባ "ሲንዶቆዶቁ" ተስተውለው ነበር አሉ""

ነፍጠኛዋን ሀገር እንመራለን በማለት በአጤው የምኒልክ ቅጥር ግቢ በነፍጥ ተቆናጥጠው "ለኤርትራ ጥብቅና" ሲሙዋገቱ ሲፈተሽ የዜና ረሃብ ላላቸው ጉድጉዋድ ቆፋሪዎች (ጋዜጠኞች) በራሱ አንድ አትሆተ-ርእስ (ብሬኪንግ ኒውስ) ነው" ሲሉ የሚሰማቸውን ትኩሳት የሚያስፈትሱ አቅቂረኞች በአንጻሩ አይጠፉም። ጎይታይ መለስ ተዚህ ቀደም "አሰብን" ለሻእቢያ አሸከመው "ካሻቸው ግመላቸውን ያጠጡበት" በማለት ለአሥመራው "ባለነፍጥ ምክር ቢጤ ቢለግሱም ወደ ነፍጠኛዋ ሀገር የሚገባውን አየሚወጣው ፍጂታ ዘጠና በመቶ በባህር ጠርዝ ዙሪያ በመሆኑ ""ወደብ" አያስፈልገንም በማለት በየመድረኩ እነ "ብጻይ አርከበ ዕቁባይ የደማቸው ዑደት እየታየ "ሲንዶቀደቁ" መስተዋሉ ነፍጠኛውን ሀገር አሬ የሚመሩት ምን ያህል "ሌጎ ሶልዳተር" (የባዕዳን ቅጥረኛ ወታደሮች) ለመሆናቸው አንድ ምስክር ይሆናል" ሲሉ የሚያትቱም አንጠረኞች አሉ።

ሰንበትበት ባለው ጊዜ አሁንባልጠፋ ስም"ዥግናውንለምንስዬይሉታ...? በምለት ጉምጉም ስንል ከርመን ነበር። በትግርኛ "ስዬ" ማለት "ቄጤማ" የሚለውን የአማርኛ ቁዋንቁዋ ጥሬ ትርጉም ይሰተናል። በደራሲው ማስታወሻ አዲሱ መጣጥፍ ላይ ታዲያ የቄጤማውን (የብጻይ ስዬ አብርሃምን) ትክክለኛ ስብእና በመፈተሽ ደራሲ ተስፋዬ ገ/አብ "ጦቢያ" የሚለው ስም "የተምቤኑን ባለነፍጥ" እንዴት አድርጎ እንደሚያንገሸግሸውና ገናከመንደርተንነት አስተሳሰብ ያልጸዳ "ትግራይዋ ወይካአ ሞት ...!" (ትግራይ ወይ ሞት!) ከሚለው ቅዠቱ ያልነቃ በመሆኑ "በአንድነት" ሽፋኑ "አንድነት" ፓርቲን ተቀላቅሎ ሠርጎ በመግባት የአንድነት ሃይሎች አደጋ ላይ እንዳይወድቁ የቀድሞው "የቤት ልጃቸው" በደራሲው ማስታወሻ ላይ "ሁለቱ ዝሆኖች ሲጣሉ ብቻ ሳይሆን ሁለቱ ዝሆኖች ሲሳረሩ(ሲፋቀሩ) ጭምር የሚጎዳው ሣሩ ነው" በማለት ምክር ቢጤ በማኖሩ "የተምቤኑን ባለነፍጥ" ዲስኩሩንለመስማት ሃያና ሠላሣ ዶላር እየከፈልክ በስብሰባ ደጅ የምትጠና ነፍጠኝ አሁላ "ጎድን ...ለወያኔ ..! " በምለው አቁዋምህ በርትተህ በአጽንኦት መታገል አለብህ።" በማለት የሚያሰምሩ ሃተተኞች ይደመጣሉ። ተዚህ ቀደም ኬክ ቤቱን፣ ጋራዡን< ወፍጮ ቤቱን< ሆቴሉን እንዳለ በመቆጣጠር "ለወያኔና ለሻዕቢያ" መረጃ ውስጥ ውሥጡን በማቀበል ልዋጭ ልዋጭ እየተባለ ነፍጠኛዋን ሀገር ብዙ ጉድ አድርገዋታልና ጠንቀቅ ነው..! የሚሉም አቃቂረኞች አሉ።

በቅንጅት የምርጫ ወቅት ሰሞንኛ ከፊሉ "የሀዲሽ ዕምባባ" ህዝብ ለቀድሞው የከተማይቱ ነጋድራስ "ለአርከበ ዕቁባይ" መዲናዋን ጎንበስ ቀና በማለት ለማሳመር ደክሙዋል" በሚል ግንዛቤ የተለያየ አስተያየት ቢያደርጉላቸውም "ዛፉን ለመገርሰስ ቅጠሉን መበጠስ" ፋይዳ የለውም። ወያኔ ምን ጊዜም ወያኔ ነው...! በሚል አቁዋምበምርጫ ካርድ ነፍጠኛው በካርዱ ስለዘረራቸው ማልዶ ላይ ጎጆውን ቀልሶ ምሽት ላይ ሲደርስ ቤቱ ፈርሶ የሚጠብቀው አንዳንድ ነፍጠኛ፡-

... አርከበ ሱናሜው ነፍስህ አይማር እንደወፍ አሞራ ከዛፍ እንደር..?

በማለት ቢቸግረው ራሱን በመጠየቅ አቤት..! ማለቱ አልቀረም" የሚሉ ትውስታዎች "የቴሌቪዥን ውይይቱን" ምርኩዝ በማድረግ የአርከበ ሱናሚውን "ነፍጠኛዋ ሀገር ወደብ አያስፈልጋትም" የሚለውን የጎይታይ መለስን አቁዋም በማራመዳቸው "ወያኔ ምን ጊዜም ወያኔ ነው...!" የሚሉም ሀተተኞች አሉ። በነገራችን ላይ የፓርላማው አፈ-ንጉሥ"እምባሰደር ተሸመቶ" ለተቃዋሚው በህገ-መንግሥቱ ዲየንብ እየተባለ ስደት እንደቆሎ እየቆነጠሩ የነፍጠኛውን ህዝብ ህይወት የሚነኩ ጥያቄ ሲነሳ በቆመጥ ዱላ ጠረቤዛ እየደበደቡ ሲገድቡ ነፍጠኛው በሚቆርጥላቸው ደመወዝ ይሆን? ሁለት ዘመናዊ ሰቀላ ቤቶችን ለፈረንጅየሚያከራዩት አሊያስ በስፖርት ፌዴሬሽን እያሉ በድርሻቸው እሳቸውምበጀመሩት "የአየር በአየር ንግድ" በሙስናትድግና ዘና ብለው የሚኖሩት...? ሲሉ የሚጠይቁም ክፍሎች አልጠፉም።

የሰሞኑን የጎይታይ መለስን "ዲስኩርናማስፈራሪያ" በተመለከተ "አዲስ ነገር አይደለም" በማለት በአፍሪካ ውስጥ ጋጠወጥና ሥነ-ምግባር የጎደላቸው ነፍስ ገዳይ መሪዎች በሚዲያ ላይ እየቀረቡ "ያዙኝ ልቀቁኝ" ባይነታቸው ጀንበር ስትጠልቅባቸው ደግሞ ደብቁኝ ደብቁኝ ማለታቸው አይቀሬ ነው" ሲሉ በማስመር "ወዲ ዜናይ ሲናገሩ እሳት ናቸው ..!" በማለት አንዳንድ ደንገጡሩዎቻቸው "ማስተዛዘኛ" ሲሰጡዋቸው መደመጡን በተመለከተ "በመሸታ ቤትን አዲፕሎማሲያዊ ቁዋንቁዋ" መካከል ልዩነት እንዳለ ያልተረዱ ራሳቸው "በመሸታ ቤት ቁዋንቁዋ" የተጸዳዱ መሆን አለባቸው" በማለት የሚሰማቸውን "ትኩሳት" የሚያስለኩ ሃቲተኞች አይጠፉም። የቀድሞው ፕሬዚዳንት ኮሎኔል መንግሥቱ እንኩዋን አንዳንድ ጊዜ ቶምቤ "ዘብረቅ" ካላለባቸው ጥሩ ጥሩ ቃላት የሚያቀርቡላቸው እንደ ሽመልስ ማዘንጊያ ያሉ ራፖርት ጣሃፊ ስለነበራቸው ወዲ ዜናይም "ንግግር አሳማሪ አንድ አማካሪ ቢኖራቸው በነፍጠኛው ዘንድ ከሃሜት ይድናሉ" ሲሉበአጥንኦት የሚጠቁሙ ታዛቢዎች ይኖራሉ። እጀ እጅ ..! በሚል አገላለጽ "ውሉ እንደጠፋበት ልቃቂት" የተንዛዛ ዲስኩር ለንጉሥ አይገባምና "በጭዋ ቁዋንቁዋ ጭዋ ሆኖ መገኘት "መታፈር ለወንበር መታፈር በከንፈር" የሚሉም አይጠፉም ....! ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው በቅርቡ "ወደ ትግራይ ሪፓብሊክ" መቀሌ ላይ አቅንተው ነበር አሉ። ለምን ..? ሲባል የአንድነት ፓርቲን አቁዋም< ከመድረክ ጋር ያለውንም ተዕልኮ በሚል ሽፋን "በነፍጠኛው በጦቢያው ሕዝብ" ስም ይቅርታ ለመለመን። በዳይ ማነው ..? ተበዳዩስ ፥? የሚለውን ለጊዜው እንተወውና አቶ"በድሩ አደም" በግላቸው ላደረጉት "ወደ መጡበት እንመለሳቸዋለን...!" ለሚለው የቁዋንቁዋ ሀረጋቸው ፍርድ ቤት ቀርበው በነጻ ስለተሰናበቱ "ትግሬ ወደ መቀሌ ንብረት ወደ ቀበሌ በሚል ስላቅ ምጸት በአንዳንድ ወገኖች ወርዱዋል" በማለት ኢንጅነሩ ያወረዱት ዲስኩር በምንም መመዘኛ ሚዛናዊ አይደለም ሲሉ የሚያትቱ አቃቂረኞች ተደምጠዋል። ተዚህ ቀደም "ነፍስ ገዳዩ ፓስተር ታምራት ላይኔ" ጥቂት ደንገጡሮችናሰባስቦ ወደ ኤርትራ መረብምላስ በመላክ "የአማራው ሕዝብ ኤርትራ ውስጥ ላደረገው ጥፋት "ድንጊያ ተሸክሞ ይቅርታ መጠየቅ አለበት ..!" ብገማለት በሕዝቦች መካከል ቁርሾ ለመፍጠር ካደረገው የከሸፈ ሙከራ አንጻር የቅርቡ የኢንጅነር ግዛቸው ድርጊትም መሳ ለመሳ በመሆኑ "ጭምብላቸውን" እየቀየሩ መስለው የሚቀርቡት "ኢንጅነር" የብዙ ታዛቢዎችን ቁጣ አስከትለዋል" ሲሉ የሚያሰምሩ አቃቂረኞች ይደመጣሉ አሉ።

ራሱን አለቃ< ባላንባራስ< ኣንጥራር ...! አቤት..! አቤት ..! የሹመት አበዛዝ..!) እያለ እንደባህታዊ ፀጉሩን አገልድሞ የመሰለውን የሚያቀልም አንድ ወገኛ "አለቃ ተክሌ" ነኝ ባይ ግለሰብ "የተሸነፍነው በትግራይ የምንድነውም በትግራይ ..!" እያለ የጥላቻ ጭቃ በማቡካት "ትግራይን አወድሶ ሌላውን ወገን አኮሦ" ማቅረቡ " የጥላቻ መጋረጃ" ከመክፈት በስተቀር ከቶ ሌላ ምን ሊፈይድ..? በማለት ጉም ጉም የሚሉ ወገኖች አይጠፉም። "መታፈር በበዕር፣ መታፈር በከንፈር..! ይሉዋል ይሄ ነው ሲሉ የሚያብጠለጥሉ ሌሎች ክፍሎችም ይደመጣሉ። አረጋሽን ለአድዋ፣ ተምቤንን ለስዬ ያሸከመው ባላንባራስ ተክሌ በሹመት በሽልማቱ በኩል ሁላችንም በድርሻችን "የጎጸ ባንዴራችንን በየደጃፋችን እንድንተክል" ቢያበረታታም "የደራሲው ማስታወሻ" ስደተኛው የነፍጠኛዋ ሀገር አስታዋሽ ግን "ስዬን አትመኑ..!" ስዬንከማመን አንድ ቁና ደማሚት ላይ መቀመት ይመረጣል " አይነት ማስጠንቀቂይ አይነት ምክር በመስጠቱ "አንድነት ፓርቲን" የጠለፈው የቀድሞው የመከላከይ ዓበጋዝ "የቡርቱካንንና የአሰብ ወደብን ጥያቄ ካርድ የያዘው ለዘዴ/ለስልት/ ነው የሚል ሌላም ጉም ጉምታ ስለሚሰማ ነፍጠኛ የተባልክ ሁላ " ጎድን ወያኔ..! ጎድን ቄጤማው.! ስዬ አብረሃም ..! ማለት አለብህ" የሚሉም ሃተተኞች በምርጫው ዋዜማ ላይ ይደመጣሉ"" ኦሮማይ ...!




Tikam K. Lalla, LL.B.

• BARRISTER • SOLICITOR • NOTARY PUBLIC

• ኢሚግሬሽን • ቪዛ • የህግ ውክልና

• House Purchase/Sale/ Mortgages
• Wills • Incorporation • Business
• Immigration • Visa • Declarations
• Power of Attorneys • Notarizations

ቲካም ኬ ላላ፥ የህግ ጠበቃ

Toronto Main Office:
1203B Bloor St. W., Toronto, ON, M6H 1N4
(Between Lansdowne & Dufferin)
Tel: 416-532-2801 • Fax: 416-532-4942
email: tklalla@rogers.com

Mississauga Home office:
5159 Hidden Valley Court
(Eglinton & Creditview)
Tel: 905- 812-8004
(Evening & Weekends - By appointment only)

# ከ ዜ ና ው ባ ሻ ገ ር

ከገጽ 15 የዞረ

ባለበት ቢያንስ በምርጫው አንገባም እኳ መሪያችን ሳትፈታ ማለት ሲገባ በዝምታ ሳይሆን ያውም

በይፋ ተፈታች አልተፈታች ብሎ ወደ ምርጫው ዘው ማለት በጣም አሳዛኝና ብስለት የጎደለው ለመሆኑ አንድና ሁለት የለውም:: መሀንዲስ ግዛቸው ይፈቱ የምንለው የራሳችንን የቅንጅት

እስረኞች እንጂ ስለሌላው አያገባንም ብለው በራዲዮ መግለጫ የሰጡ መሆናቸውን ስናስታወስ ፕሮፌሰር መስፍን ደግሞ ደብዛቸው ስለጠፋ የኢሕአፓ መሪዎችና አባላት ትንፍሽም አልል ያሉና አንዲትም ቀን የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ብለው ያልተሰለፉ መሆናቸውንም ማስታወስ

የግድ ይሆናል:: አንደምታ ለየግላችን:: ይባስ ብሎ ግን መሪው የታሰረችበትና ከብልጥ ጠባቦች ጋር የተቀናጀን ድርጅት በንትርክና በግብገብ መከፋፈልና በቡጢ ደረጃ አዛውንቶቹ ሳይቀሩ

እርስ በርስ መደባደብና ሹም ሽረት ማካሄድም ድርጅቱን መሳቂያ አድርጎ በመጥፎ ሁኔታ ያለችውን መሪያቸውንም ልብ የሚያቆስል ግን ወያኔን የሚያስፈነድቅ ነው:: ድርጅቶች መከፋፈል

ሲመጣባቸው ቀኑ ደርሷል እንዲሉ ከመከፋፈል ባይድኑም በተቻለ መጠን ጊዜን መምረጡ፤

መለስተኛ ቅራኔውን በዚያው በረገበ ደረጃ ለመያዝና ድርጅቱን በሞላ ቅሌት በማያላብስ ሁኔታ ሂደቱንም ለመደምደም በተጣረና በተገባም ነበር:: ይህ ግን ሁሌም አይሳካም፤በየድርጅቱ የተከሰቱ ማፈሪያ ክህደቱዎችና አንጃዎች መኖራቸው ይህን አረጋጋጭ ነው:: ከነዚህ ሌላ በወያኔ ዙሪያ የተኮለኮሉት የምርጫ አጀቦች ለግምገማም የሚበቁ አይደሉም:: ህጋዊነት የተነፈጉትም ቢሆኑ ወደፊት ሲሉና ሲጠናከሩ እያየንአይደለንም:: ከወደ አስመራ ብቅ ይላል የሚባለው ግንባር በመጀመሪያ ደረጃ ሁሉን መታቀፍ የሚገባቸውን አቃፊ ሳይሆን ሻዕቢያን የማይጎረብጡትን ስብሳቢ ሊሆን የታሰበ ከመሆኑ ሌላ በጥር እወለዳለሁን ሲል ተደምጦ እስካሁን በአልወለድም ቀይሮታል:: ቢወለድም ብዙ ዕልልታ አሰሚ የሚኖሮ አይመስልም:: አነግም ተፋዟል ብንል ማጋነን አይሆንም:: በአንጃ ተጠቅቶ የነበረው ኢሕአፓ የተባለው አንጃ አርስ በርሱ ሲባላና ለሁለት ሲከፋፈል (አንጃዎቹ ድርጅቱ በሰርጎ ገብ ከፋፈለን ባይ ናቸው) ለማየት ቢበቃም የራሱን እንቅስቃሴ በተመለከተ በይፋ ከሚታዩትና ከሚያስተላልፋቸው አዋጅና ጥሪዎች ባሻገር ይህ ነው የሚሉ ታዛቢዎች የሉም:: ምስጢሩ ዝግ እንደሆነ አለ:: ወያኔ ግን መፍራት መስጋቱ አልቀረም::

ለዚህ ለወያኔ መርበትበት ተጠያቂው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው:: ይህ ሕዝብ ገገርዎችን ባልጠበቁት ጊዜና ሁኔታ ማስደንገጥ ልምዱ ነውና (የካቲት 66፤ ግንቦት 1997) መለስ ዜናዊ ምርጫውን

ቆልፌና ለስርቆት ጭኜ ጨርሻለሁ ቢልም ሕዝብ እዳያስደነግጠውና ጉድ እዳይፈላ ይሰጋል::

ሕዝብ በወያኔ ላይ ያለውን ያመረረ ጥላቻ በቅድሚያ የሚያውቀው ወያኔ ራሱ ነው:: የወያኔ ጥርቅምን ድክመት አሳምሮ የሚያውቀው ራሱ የወያኔ ገገር ቡድን ነው:: የጨለመ ሁኔታ መኖሩና ሕዝብም ካመቸው ወያኔን ለአንዴም ለሁሌም ሊያደባይ ሊነሳሳ መቻሉንም ወያኔ ጠንቅቆ ያውቃል፤ ይፈራዋልም:: ለዚህም ነው በፖሊሱና በወታደሩ ዘንድ ሹም ሽሩና አማራ ኦሮሞውን ወይም ከክልል 1 ያልሆነውን ምንጠራው የተፋፋመው:: መለስ ዜናዊ ታማኝ የሆኑትንም መኮንኖቹን በዋና ዋና ከተሞች ሁኔታውን እንዲቆጣጠሩ አሰማርቷል፤ ካስፈለገ አፈና እንዲያካሂዱ ለማለት ነው:: መለስ ዜናዊ የጠበቀውን ድል የሚያገኝበት መንገድ ቀላል ይሁን ውስብስብ በመጪው

15 ቀናት በሕዝብ እንጂ በራሱ የሚወሰን አይሆንለትም::

ይህን ከዘረዘርን በኋላ ደግሞ እስቲ የሚከተሉትን ዕይታ እንስጣቸው፤

ጋዜጠኛ ነኝ ባዩ ተሰፋዬ ገብረአብ ከዚህ በፊት በፃፋቸው መፅሀፍት (ተራራ ያንቀጠቀጠ ትውልድ፤ የቡርቃ ዝምታ፤ የእፎይታ ርዕሰ አንቀፆች ወዘተ) ብዕሩ ለጉልበተኛና ባለገንዘብ የሚሸጥ መሆኑን በማያወላዳ መንገድ ያስመሰከረ ነበርና በአሁኑ ደራሲው ማስታወሻው ደግሞ ብዕሩን ለሻዕቢያ ሸጧል ወይ ብለው ጠያቂዎች ጥቂቶች አይደሉም:: ቢሾፍቱ ቢሾፍቱ ቢልም ይህ የኤርትራ ተወላጅ ዶክተር ነጋሶ እንዳሉት ከመመህሩ ደቀመዝሙሩ ዓይነት ከማንም ኦሮሞ በላይ ኦሮሞ ነኝ (አያይዞም ፀረ አማራ ነኝ) ሊል ቢነሳም የአሁኑ መፅሀፉ ሻዕቢያ በሚጠላቸው በስየ አብረሃ፤ በገብሩ አስራትና መሰሎቻቸው ላይ ጠንከር ማለቱ የነዚህ አፍቅሮ ያለባቸውን ሰዎች ጥላቻ አትርፎለታል:: የኢትዮሚዲያ አዘጋጅና የትግራይ ትምክህተኛነት አንፀባራቂ ነው በሚባለው በአብርሃም በላይ (ይህን ግለሰብና ወያኔያዊ ሚናውን ተስፋዬ በ " ዜጠኛው ማስታወሻ" አጋልጧል) ድረ ገፅ ላይም ብዙ ሂስ በተስፋዬ ላይ በመውረድ ላይ ነወ:: ሌሎች ደግሞ የደራሲውን አፃፃፍ ከማድነቅ በተጨማሪ ስለነ ገብሩና ስዬ የተፃፈውም ሁሉ ሀቅና ተገቢ ነው ብለዋል:: በዚህም በዚያም ግን የግለሰቡ መፅሀፍ መወያያ ሆኗል፤ ለደራሲውም ትርፍ ሳያስገባ እንደማይቀር ይገመታል:: ከዚህ በተያያዘ ደግሞ የቀይ ሽብር አልታወጀም ባዩ የዶክቴ/ ሀይሉ አርአያ ሊቀ መንበርና ጌታ የነበረው መንግስቱ ኃይለማርያም የሕይወት ታሪኩን ቅፅ 1 መፅሀፍ (ከ400 ገፅ በላይ) ለህተመት አዘጋጅቶ የሎስ አንጀለሱ የፀሐይ ህትመት ባለቤት ሊያትምለት በዝግጅት ላይ መሆኑ ታውቋል:: ከዚህ ቀደም ገነት አየለ ከመዘገበችው ውሸቱና ክህደቱ በተለየ አዲስ ነገርን ይፅፋል (ቀይ ሽብርን እኔ አላካሄድኩም ይላል እንጂ ይህ ቀለ ም የሞላ ጠርሙስ በአደባባይ ወርዋሪና ቀይ ሽብር ይፋፋም ብሎ ጯሂ እንደ አሳፋሪው ዶክተር ቀይ ሽብር አልታወጀም አላለም) ተብሎ የማይጠበቀው በሐራሬ ከተማ ከፀሐይ አሳታሚና ባለቤት ከአቶ ኤልያስ ወንድሙ ጋር ተገናኝቶ በሰፊው መወያየቱም ተዘግቧል::

– ተስፋዬ ገብረአብ በወያኔ መንም ጥቃት ሳይደርስበት በደቡብ አፍሪካና በአሰመራ መፅሀፉን ሊያዘጋጅ ዕድል ቢያገኝም ወያኔን በኢትኦጵ ጋዜጣ ላይ በኢየሩሳሌም አርአያ ስም ሲያጋልጥ የቆየው አርአያ ተሰፋማርያም ግን ልጁን ለማሳከምም በሚል በተሰደደበት በኒው ዴልሂ ከተማ በህንድ ሀገር ወያኔ በቅጥረኞች አማካይነት የግድያ ሙከራ አድርጎበታል:: አርአያ በስደተኛ ተቋሞች ምንም መከላከል ሰላልተደረገለት ችግሩን በማጋለጥና እርዳታም በማሰባሰብ ሊታደጉት በባዕድ ሀገር ያሉ ኢትዮጲያውያን ተመስጋኝ ጥረት እያደረጉ ናቸው:: ሌሎች ግን ፀረ ወያኔ ነን ቢሉም ችግርህን አልሰማንም ብለው ሳይተባባሩ መቅረታቸወም ተጋልጧል::

– አለ የለም ተብሎ ውርርድ የሚገባበት የመለስ ስጋጃ የሚባለው ሰዩም መስፍን (ስዩም ሙሳ ሲያሰኘው) የኬንያ አንድ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክተርነት ዲግሪ አግኝቶ ሲፈነድቅ ሰው ታዝቦታል:: ያው የፈረደበት ሕዝብ ደግሞ ዶክተር ስዩም ማለት ግድ ሊሆንበት ነው፤ እንደ ቀዳማይ እመቤት በሉኝ ባይዋ ጉደኛ:: ሀቁ ሲመረመር ግን ስዩም መስፍን ለዩኒቨርስቲው የማይናቅ የገንዘብ ድጎማ (ጉቦ) ከፍሏል የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም::

– የኢትዮጵያ ሕዝብ የጎደለው ሌላ የቢራ ፋብሪካ የሆነ ይመስል የወያኔ ጄኔራል የነበረው የራያ ተወላጅ ፃድቃንና የ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ከበርቴው ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ በራያ መሬት ምንም ሊዝ ወይም የመሬት ክራይ ሳይከፍሉ በተሰጣቸው መሬት ላይ የራያ ቢራ ፋብሪካን መገንባት ጀምረዋል:: ራያ ድርቅ ቢያጠቃውም ቢራው ሊፈስለት ነው ማለት ነው!!

– ኢሕአፓን እያሳደደ የወጋውና በትግራይ ምድርም በቀይ ሽብሩ የተሳተፈው ወያኔ የአዞ እንባውን በመርጨት የቀይ ሽብር ሀወልት፤ ቀብር ወመዘክር እያለ ሊመፃደቅ መሞከሩ ምንም የፖለቲካ ትርፍ እንዳላስገኘው ታውቋል:: ለለየለት የወያኔ ዘረኛ ዘፋኝና ነፍሰገዳይ ኢያሱ በርሄም በትግራይ የ11 ሚሊዮን ብር ሀውልትና ቤተ መፃህፍት ሊሰራ መወሰኑን አሳውቋል:: ሕዝብ እየተራበና እየተሰቃየ ባለበት ለዘረኛ ዘፋኞችና ታጋይ ተብዬዎች ሀውልት እየተባለ የሀገር ገንዘብ በመባከን ላይ ነው:: ቀይ ሽብር ከተባለ ደግሞ ለሰማዕቱ ወያኔ ሀወልት ሊሰራ የሞራል ብቃት ከቶም እንደሌለው ሁሉም ዜጋ ያውቃል::

– የኢትዮጵያ ወጣት ሴቶች ወደ መካከለኛ ምስራቅ እየተላኩ ለዘረኝነትና በደል ተጋልጠዋል ተብሎ የተወገዘ በመሆኑ ወያኔ በመጋለጡ ለሽፋን አንዳንድ ጫጫታን ካሰማ በኋላ ግልፅ በሆነ አልሸሹም ዞር አሉ እነሆ ወጣት ሴቶችን ወደ ኩዌት ለመላክ ከዚች አረብ ሀገር ጋር ስምምነት ተፈራርሟል:: በኩዌት የተሻለ ሁኔታ አለ ብሎ ሊያታልል የሚጥረው ወያኔ ሊደብቅ የማይችለው ሀቅ ግን ሌባኖስና ኩዌት "ከዝ ንጀሮ ቆንጆ ምንይመራርጡ " መሆናቸውን ነው:: በኩዌትም ቢሆን የባዕድ ሰራተኞች ብዙ ችግርና ቀፋፊ ዘረኝነትን እየተቀበሉና እየተሰቃዩ ናቸው:: ወያኔ ህፃናትን ለጉዲፈቻ መስጠት በሚል ሽፋን አሁንም ህፃናትን ለባዕዳን በገፍ እየሸጠም መሆኑ መጋለጥ፤ መወገዝ አለበት::

– የወያኔ ሚሊሺያ ከሚሪሌ ተነስቶ ወደ ኬንያ በመዝለቅ በቱርካና ሀይቅ ዶጊያግ በተባለ ቦታ የነበሩ 200 የኬንያ አሳ አጥማጆችን አባሮ ቦታውን መያዙን በማውገዝ የኬንያ ቃል አቀባዮች አጋልጠዋል:: ሌላ የውጊያ ግንባር ሊመጣ ነው ደግሞ?

– ኢንጂነር ግዛቸው በወያኔ ፍርድ ቤት ፕሮፌሰር መስፍንንና ተከታዮቻቸውን ከሰዋል:: ፕሮፌሰኗ መስፍን ደግሞ ህጋዊው የብርቱካን ተከታይ እኔ ነኝ ባይ ሲሆኑ ተከታዮቻቸውን በጎረምሶች በአጠና ይኸው ኢንጂኔር ማስደብደቡን ጠቁመዋል:: ፍርድ ሰጪ ማን? ወያኔ! ቅራኔውን በአግባብ መያዝ አቅቶት ብለው ያን ትውልድ የሚወርፉት ሁለቱ አዛውንት መሰረታዊ የአስተሳሰብ ልዩነት እንኳን ሳይኖራቸው ወደ ቡጢና አጠና ድብድብ መድረሳቸው የሚያስተዛዝብ ነው:: ዕድሜ ይስጠን!

– ባለፈው መብራት ሀይል/ኮረንቲ/ በሌለበት ሀገር የኤሌክትሪክ መኪና ተሰራ ብሎ ወያኔ ሲያሰቀን ነበር:: አሁን ደግሞ ባለፎቅ አውቶቡስን ላመርት ነው ይላል፤ በሆላንዶች እርዳታ:: ከዚህ በፊት እነዚሁ ሆላንዶች ለመለስ ዜናዊ በቀጥታ ጉቦ አፍሰው ግልጋሎቱ ወይም መሰራቱ ያቆመ ፎከር አይሮፕላን ለአየር መንገዱ ሸጠው እንደነበር የሚታወስ ነው:: የጣሊያኑ ሳሊኒ አለ ጨረታ ኮንትራት እየተሰጠው /ጉቦ ከፍሎ/ እንደሚሰራው ፈራሽ ግድብ ማለት ነው:: መቀለጃ! በግርግሩ ግን የወያኔ ባለስልጣኖች ኪሳቸውን ያደልባሉ::

– በአሜሪካ የወያኔ አምባሳደር የነበረው የሳሙዔል አሰፋ ሚስት እመቤቴ ብላ ከተጠጋቻት አዜብ ጎላ በመጣላቷ የተነሳ ሳሙዔልም ሚስቱም ተገልለው በሁሉም መስክ ክስረትና ችግር እንደገጠማቸው እየተነገረ ነው:: ሳሙዔልም ስራ ማግኘት ከብዶታል ተብሏል:: ወያኔ ለወዳጁ እሳት ይዟል በእጁ!

በሉ ወገኖች በሚቀጥለው ስንገናኝ የወያኔን ቀውስና ያርገውናም ውድቀት ቸር ወሬ ያሰማን!!

# የተሳካ ጉባኤ ተካሄደ

**ከገጽ 5 የዞረ**

በማመን ስብሰባው በደስታ ተጠናቅቆ ተበተነ። ከዚህ ላይ እስካሁን ሲያገለግሉ የቆዩትና የሥራ ዘመናቸውናጠናቀው የተሰናበቱት የቦርድ አባልት ትልቅ ምስጋናና ክብር ይገባቸዋል። ስብሰባውንበትክክል በመምራታን ሃላፊነታቸውን ለተተኪው ባግባቡ ማስተላለፍ በመቻላቸው አበጃችሁ፡ ኮርተንባችሁዋል ሊባሉ መቻል አለበት።

የማህበሩ መጀመሪያም መጨረሻም ከፍተኛ ችግሩ ነው የሚባለው ጥለናት በመጣነውና በህሊናችን ውስጥ ዘወትር የምትመላለሰው ሀገራችን ፖለቲካዊ ሁኔታ ነው። ሀገር ውስጥ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ በሞቀና በበረደ ቁጥር በውጭ ሀገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ተቁዋማት ላይ ችግር መፍጠሩ አልቀረም። ይህም በመሆኑ ከደርግ ሥርዓት ጀምሮ አስካሁን በቶሮንቶ ውስጥ የሚገኘውን ይህን ትልቅ ማህበር እንዳመሰው አለ። ሁኔታው በሦስት ዋና ዋአን ዘርፎች ሊገለሽ ይችላል፡- አንደኛ) ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ሁኔታ እንደፍላጎታቸው ለመደገፍና ለማገዝ ማህበሩን እንደመድረክ ለመጠቀም የሚሹ ወገኖች በመኖራቸው፤ 2ኛ) ማህበሩ በምንም መንገድ ከሀገር ቤቱ የፖለቲካ ሁኔታ ጋር መያያዝና መጠቀሚያ መሆን የለበትም የሚል ጠንካራ አቁዋምያላቸው ወገኖች በሌላ በኩል በመቆማቸው፤ 3ኛ) ማህበሩ ገለልተኛ ሆኖ በየትኛውም ቦታና ጊዜ በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን ላይ ለሚደርስ ማንኛውም የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መጣስ በግንባር ቀደምትነት መሰለፍ ይኖርበታ የሚሉት ዋና ዋና መሙዋገቻ አቁዋሞች ሲሆኑ በመካከሉ ግን ከዚህም ከዚያም እንዳመችነቱ እየተገለባበጡ ከላይ የተጠቀሱትን የበሰሉ የአመለካከት ልዩነቶችን በመጠቀም ማህበሩን በቅራኔ ወጥረው የግል ጥቅማቸውን ለማሳደድ የሚሹና ነገን የማይመለከቱ የዛሬ ሰዎች መኖራቸው ሊታወቅ ይገባዋል የሚሉ አሉ። የልዩነቶች መኖር ከቶ ባልከፋ ነበር፤ ችግሩ በማህበሩ ውስጥ በየአመለካከቱ ቦድኖ ትክክል የሆኑም ያልሆኑም ዘዴዎችን በመጠቀም ሌላውን ክፍል በማግለል ማህበሩን ለመቆጣጠር የሚደረገው ግፍጫ ነው ሲሉ የሚያሰምሩ አሉ።

ሐዋርያ ጋዜጣ እንደብዙሃን መገናኛነቱ በማህበረሰቡ ወስጥ የሚነሱ የተለያዩ ጉዳዮችን በእኩልነት ቦታ ሰጥቶ ማስተናገድ ግዴታው ቢሆንም፣ ይህን ሙያዊ ግዴታውን እያከበረ ይበጃል የሚላቸውን አቅጣጫዎች በርዕሰ አንቀጹና በልዩ ልዩ የጋዜጣው መልዕክቶች ላይ ያንጸባርቃል። በቶሮንቶ የኢትዮጵያዊያን ማህበርን በተመለከተ በተደጋጋሚ በርዕሰ አንቀጹ ዙሪያ ይሻላል ያለውን ጠቁሙዋል። ቅንነት በተሞላበት ሁኔታ ለማህበረሰቡና ለሀገር ቤቱ ሕዝባችን ይጠቅማል ከሚል በልዩ ልዩ የሃሳብ አውታሮች ላይ አቁዋም ያላቸውን ወገኖች እያከበረና አቁዋማቸውን እያስከበረ ለሚሻለው ወገን አንድ ድምጽ ለመሆን ግን ለራሱም ዴሞክራሲያዊ መብት ይታገላል። ስለሆነም ሐዋርያ የኢትዮጵያዊያን ማህበር ገለልተኝነቱን ጠብቆ የትም ይሁን መቸ የኢትዮጵያዊያን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሲጣሱ ቀድመው ከሚደርሱት ውስጥ አንዱ መሆን አለበት የሚሉትን ወገኖች አቁዋም ይደግፋል። ማህበሩን የቡድን አመለካከት ማራመጃና መጠቀሚያ ለማድረግ የሚታሰብን ጥረት አጥብቆ ይቃወማል። ምክንያቱም አንደኛ ዴሞክራሲያዊ ሂደትን ይጥሳል፤ ሁለተኛም በምንኖርበት ቦታና ጊዜ ውስጥ ድርጊቱ ህጋዊ አይደለም። ማህበሩ በውጭ ሀገር የምንኖረውን ነው ማገልገል ያለበት የሚሉ ውገኖች ሃሳባቸው ግማሽ እውነት ነው ማለት ትክክል ነው። በውጭ የምንኖረውን ከትውልድ ሀገራችን ነጥሎ መመልከት ለሀገራችንና ለሕዝባችን ዛሬ በበኩላችን ልናደርግ የምንችለውን አስተዋጳኦ ከመገደቡም ባሻገር ቀጣዩን ትውልድ ያልተመለከተ የአመለካከት ዝንፈት አለበት። ከማህበሩ አላማዎች መካከል አንዱ ኢትዮጵያዊነት ወግና ባህል እንዳይጠፋ መንከባከብ፣ በማህበረሰቡና በሌሎች መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ ማገልገል ነው። ቢያድለንማ፤ በህዝብ አመኔታ የተቀመጠ ዴሞክራሲያው ሥርዓትና መንግሥት ቢኖረን ኖሮ በየጊዜው በትዮጵያ ኤምባሲዎችና አቆንሲሎች አመካይነት ልዩ ልዩ ዝግጅቶችንና ፕሮግራሞችን በመዘርጋት ከሀገራችን ጋር ሊኖረን የሚችለው ጥብቅ ግንኙነት የበለጠ ማዳበር ነበር።

ለማንኛውም ተከባብረንና ያንዳችን ሃሳብ ለሁላችን፣ የሁላችን ለያንዳንዳችን ይበጃል ከሚል በጎ መንፈስ ተነስተን በብዙሃኑ ድምጽና ፍላጎት እስከተገዛን ድረስ ከቶ የማንደርስበት ዕድገት የለምና ይህን በልቦናችን ያሳድርልን በማለት እናጠቃልላለን።




# Looking forward to going back?

**Lufthansa announces extended service to Addis Ababa with additional connections on Ethiopian Airlines**



This summer, Lufthansa makes it easier to share the rich history and colorful traditions of Ethiopia with the people you love: 13 months of sunshine, the sound of drumbeats announcing an afternoon service, the aroma of coffee beans roasted as you wait, and gathering with family to tear the injera and dip it in your favorite sauces.

Lufthansa announces extended service to Addis Ababa with additional connections on Ethiopian Airlines. To get there in comfort, we provide daily service from Toronto to our hub in Frankfurt, where quick, seamless connections to Bole International Airport (ADD) are available ten times per week, some made possible through our partner, Ethiopian Airlines.

**Like you, we have roots in Africa**

To offer this expanded timetable, we've partnered with Ethiopian Airlines, the flag carrier of Ethiopia. Ethiopian Airlines has grown to become one of the continent's leading carriers.

Lufthansa is proud of its forty-year history of service in Ethiopia and is very pleased that an increased demand has allowed for an expanded flight schedule.

The route will be served by an Airbus A340-300, offering exemplary service and excellent entertainment on personal video screens in all three classes. Choose from a wide selection of current films, audio books or music at the touch of a button, right from your fingertips.

Visit **lufthansa.com** now to book your journey back to Ethiopia!

There's no better way to fly.℠

Lufthansa